MARYLAND STATE DEPARTMENT OF
EDUCATION
EQUITY AND EXCELLENCE

2023



### የወላጅ ተከታታይ መረጃ

በ Maryland የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች፡-

# የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር እቅድ

የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደት | የወላጅ መብቶች | IEPን መረዳት | **የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር**



# መግቢያ

**በ Maryland የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት የወላጅ መመሪያ፤ የ Maryland ከልደት እስከ 21 ዓመት የወላጅ ተከታታይ መረጃ ክፍል ነው፤** በ Maryland የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደት እና በአገልግሎቶች ስርዓት ውስጥ ያሉ ቤተሰቦችን በ ግዛት ድረጃ ለመደገፍ የተነደፈ የሕትመት ስብስብ። ይህ መመሪያ በአካል ጉዳተኞች ትምህርት ህግ (Disabilities Education Act) (IDEA) ውስጥ ስላሉ የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር ሂደት መስፈርቶች የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ፤ እንዲሁም አወንታዊ ውጤትን ለማሳካት የሚመከሩ ስልቶችን እና ግብዓቶችን ይሰጣል።



# የማውጫ ሰንጠረዥ


ገጽ 4

**የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር እቅድ፡-**

ገጽ 5

**የወላጅ እና የተማሪ ተሳትፎ**

ገጽ 7

**የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር ደረጃዎች**

ገጽ 16

**ተቀዳሚ 10 ነገሮች**

ገጽ 22

**ጥያቄዎች ካሉኝ ወይም እርዳታ ቢያስፈልገኝስ?**


ለበለጠ መረጃ ይጎብኙን

**www.marylandpublicschools.org**

# እንኳን ደህና መጡ
# ወደ Maryland የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር እቅድ

### የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር እቅድ ምንድን ነው?

**የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር እቅድ፤ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ለህይወት የሚያዘጋጅ ቀጣይነት ያለው ሂደት ነው።** ይህ ሂደት የሚጀምረው በልጆች ቀደምት ህይወት፤ ስለ አካባቢያቸው፣ ስለ ሚወዷቸው፣ ስለ ሚጠሏችው እና ስለ ፍላጎቶቻቸው ሲያውቁ ነው። የተማሪዎችን የወደፊት ራዕይ እድገትን በሚደገፉ እና ወደ አዋቂ ህይወት ለማሸጋገር በሚያዘጋጁ ተሞክሮዎች ውስጥ እያሳተፉ በሁሉም የትምህርት አመታት ይቀጥላሉ።  የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር እቅድ ተማሪዎችን፣ ቤተሰቦችን፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞችን እና ሌሎች አስፈላጊ የማህበረሰብ አባላትን የሚያሳትፍ የትብብር ጥረት ነው።

የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት የሚያገኙ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች፤ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወደ አዋቂነት ህይወታቸው የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ የሚደግፉ ተገቢ የሆኑ የሽግግር አገልግሎቶችን፤ በፌደራል እና በግዛት ህጎች መሰረት የማግኘት መብት አላቸው።  Maryland ውስጥ፤ መደበኛ የሁለተኛ ደረጃ የሽግግር እቅድ በ IEP ሂደት 14 ዓመት ላይ፤ ወይም አስፈላጊ ከሆነ ቀደም ብሎ ይጀምራል።  በ Maryland በ16 ዓመት እድሜ መደበኛ የሽግግር እቅድ ለመጀመር ከፌዴራል መስፈርት በላይ አልፏል። የሽግግር እቅድ በ14 ዓመት እድሜ እንዲጀመር Maryland ይጠይቃል፤ ይህም ተማሪዎች የድህረ-ሁለተኛ ድረጃ የግብ ምርጫዎቻቸውን እንዲመረምሩ እና በሽግግር ተሞክሮዎች ላይ በመመስረት እንዲቀይሩ ያስችላቸዋል።

# ህጉ ምን **ይላል**

## IDEA ምንድን ነው?

**የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ህግ (IDEA) በመላው አገሪቱ ውስጥ የአካል ጉዳተኛ ልጆችን አገልግሎቶች የሚያረጋግጥ የፌደራል ህግ ነው።** IDEA፤ የሽግግር አገልግሎቶችን ከትምህርት ቤት ወደ ድህረ-ትምህርት ቤት እንቅስቃሴን የሚያበረታታ ለልጆች የተዘጋጀ "የተቀናጁ የእንቅስቃሴዎች ስብስብ" በማለት ፍች ያስቀምጣል።  እነዚህ አገልግሎቶች የሽግግር እድሜ ላይ ያሉ ተማሪዎችን ለድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ስራ፣ ትምህርት ወይም ስልጠና እና ራስን ለቻለ ኑሮ ለማዘጋጀት የተነደፉ ናቸው።  እነዚህ እንቅስቃሴዎች በተማሪው ፍላጎቶች፣ ምርጫዎች፣ ጥንካሬዎች እና የሚያስፈልጓቸው ነገሮች ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

# የወላጅ እና **የተማሪ ተሳትፎ**

## በሁለተኛ ደረጃ የሽግግር እቅድ ውስጥ የወላጅ ሚና ምንድን ነው?

ወላጆች የልጃቸውን የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር ለማቀድ መሳሪያ አጋዥ ናቸው። ውጤታማ እና ትርጉም ያለው የሽግግር እቅድ ለማዘጋጀት ለ IEP ቡድን ወሳኝ መረጃ ይሰጣሉ። ወላጆች በሽግግር ዕድሜ ላይ ያለ ልጃቸውን በሽግግር እቅድ ሂደት ውስጥ፤ ንቁ ሚና እንዲወስድ፣ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን ችሎታ እንዲያዳብር እና የወደፊት ሕይወቱን በባለቤትነት እንዲይዝ ማስቻል እና መምራት ይችላሉ።  በወላጆች እና በአስተማሪዎች ድጋፍ፤ ተማሪዎች ፍላጎቶቻቸውን ይመረምራሉ እናም ከድህረ-ትምህርት ግቦቻቸው ላይ ለመድረስ የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን እና ነፃነትን ያዳብራሉ። ወላጆች ሂደቱን ቀደም ብለው መጀመር እና የተማሪው ድምጽ መሰማቱን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።



እንደ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፤ ልጅዎን በሚከተለው መንገድ መርዳት ይችላሉ፡-

- በ IEP እና የሽግግር ቡድን ስብሰባዎች ውስጥ መሳተፍ፤
- ጥንካሬያቸውን፣ ፍላጎቶቻቸውን እና የድጋፍ ፍላጎቶቻቸውን መካፈል፤
- ግቦቻቸውን እና ለአገልግሎቶቻቸውን አጥብቆ መደገፍ፤
- ከፍተኛ ግምት መያዝ፤
- ራስን የመደገፍ ክህሎቶችን ለመለማመድ እድሎችን መስጠት፤
- እንደ ኮሌጅ፣ ስራ እና የአዋቂ አገልግሎቶች ያሉ የድህረ ትምህርት ቤት አማራጮችን እንዲያስሱ ማበረታታት፤
- የማህበረሰብ ሽግግር ተደራሽነት አጋሮችን መደገፍ፤ እና
- የሁለተኛ ደረጃ የሽግግሩን የጊዜ ሰሌዳ መገምገም እና እንደ አስፈላጊነቱ ድጋፍ መጠየቅ።

**ራስን መደገፍ**

ራስን መደገፍ ምርጫዎችን የማድረግ፣ ችግሮችን የመፍታት፣ ግቦችን የማዘጋጀት፣ አማራጮችን ለመገምገም እና ለመብቶችዎ የመናገር ችሎታ ነው። ልጅዎቾ ስለ አካል ጉዳታቸው፣ ጥንካሬዎቻቸው፣ የሚያስፈልጓቸው ነገሮች፣ እና ለእነሱ በተሻለ ሁኔታ የሚሰሩትን ድጋፎች እና የሚስማሟቸውን ነገሮች እንዲረዱ ነው። ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወደ አዋቂ ህይወት ሲሸጋገሩ፤ እነዚህን ራስን የመደገፍ ክፍሎችን ሊማሩ እና ራስን የመደገፍ ችሎታን እንዲለማመዱ እድሎችን እና ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል።



## በሁለተኛ ደረጃ የሽግግር እቅድ ውስጥ የተማሪ ሚና ምንድን ነው?

ተማሪዎች የሽግግር እቅድ ሂደቱ ማዕከል እና በጣም አስፈላጊ የ IEP ቡድን አባል ናቸው። ተማሪዎች የመሪነት ቦታውን ቢይዙም፤ ለሽግግር እቅዱ ጉልበት የሚሆኑት ግቦቻቸው እና ምኞታቸው ናቸው።  ተማሪዎች የወደፊት ሕይወታቸውን በማቀድ ንቁ ተሳትፎ ሲያደርጉ፣ እቅዶቻቸው እንዲሳኩ የበለጠ ቁርጠኛ ይሆናሉ።

የተማሪ ሚናዎች የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- በሽግግር እቅድ ሂደት ውስጥ መሳተፍ፤
- በ IEP ስብሰባዎች ውስጥ መሳተፍ፤
- የአሁን እና የወደፊት ግቦቻቸውን ማጋራት፤
- ጥንካሬዎችን እና ተግዳሮቶችን መለየት፤
- ፍላጎቶችን እና ምርጫዎችን መናገር፤
- ከፍላጎቶች እና ከክህሎቶች ጋር የሚዛመዱ የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግቦችን መለየት፤
- ፖርትፎሊዮ መገንባት፤
- በ IEP በተለዩ የሽግግር እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ፤
- መማር፣ ኑሮ እና ሥራ ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያደርግ ጨምሮ፤ ስለ አካል ጉዳታቸው ግንዛቤ ማዳበር፤ እና
- በስራ ልምዶች ውስጥ መሳተፍ

**የድህረ-ትምህርት ቤት ስኬት ትንበያ**
በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ባለው የተማሪ የሥራ ልምድ ተሳትፎ እና ከምርቃት በኋላ ባለው ስኬት መካከል ጠንካራ ግንኙነት አለ። ከጎረቤቶች፣ ከጓደኞች እና ከአካባቢው የንግድ ድርጅቶች ጋር ትስስር ለመፍጠር የሚተባበሩ የትምህርት ቤት ቡድኖች እና ቤተሰቦች የማህበረሰቡን እድሎች ያሰፋሉ እና ልዩነቱን ያጠባሉ።



#  የሁለተኛ ደረጃ **ሽግግር ደረጃዎች**

## የተማሪው የወደፊት ራዕይ ምንድን ነው?


የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር እቅድ አላማ፤ ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ አላማቸውን እንዲለዩ መርዳት ነው። ከትምህርት ቤት ወደ አዋቂነት ለሚደረግ ስኬታማ የህይወት ሽግግር ለሚመሩ የተሞክሮ እድሎች፤ የጥናት ዘርፎችን፣ አገልግሎቶችን እና ተግባራትን ያቅዳሉ። ይህንን ለማድረግ የ IEP ቡድኑ መጨረሻውን ግምት ውስጥ በማስገባት፤ እና ተማሪዎች ስለ የወደፊት ራዕያቸውን እንዲፈጥሩ መደገፍ አለበት። አንዳንድ ጊዜ ለተማሪዎች በተለይም በሁለተኛ ደረጃ የሽግግር ሂደት መጀመሪያ ላይ፤ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ ህይወት ምን እንደሚመስል ራዕይ ማስቀመጥ አስቸጋሪ ነው። በቤት ውስጥ እና በትምህርት ቤት ውስጥ ከተማሪዎች ጋር የሚደረጉ ውይይቶች ወጣቶች እነማን እንደሆኑ፤ የሚወዱትን እና የማይወዱትን ነገር እንዲመረምሩ፤ እና ለወደፊቱ የግል ግቦችን እንዲያሳድጉ ሊረዳቸው ይችላል።

## የሽግግር ግምገማዎች

ለእድሜ ተገቢ የሽግግር ምዘና የሁለተኛ ደረጃ የሽግግር ሂደት መሰረት ሲሆን፤ ተማሪዎች ስለራሳቸው፣ ፍላጎቶቻቸው፣ ምርጫዎቻቸው እና ግቦቻቸው እንዲያውቁ ያግዛል። መለካት የሚችሉ የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግቦችን ለመለየት፤ ቤተሰብ እና ማህበረሰቡን ጨምሮ፤ ከበርካታ ሁኔታዎች እና ምንጮች መደበኛ እና ኢ-መደበኛ ግምገማዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። የግምገማ ውጤቶች ተማሪዎች በአሁኑ ወቅት እንዴት እየሰሩ እንደሆነ እና ግባቸውን ለማሳካት ስለሚያስፈልጓቸው ክህሎቶች እና አገልግሎቶች፤ ለተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ለሌሎች የ IEP ቡድን አባላት መረጃ ይሰጣል። መረጃው ተማሪዎች የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግባቸውን እንዲያሳኩ የሚያግዝ፤ አጠቃላይ የ IEP እና ትርጉም ያለው የሽግግር እቅድ ለማዘጋጀት ይጠቅማል።


## የሽግግር ምዘናዎች በ IEP ውስጥ እንዴት ይመዘገባሉ?

የሁለተኛ ደረጃ የሽግግር ምዘና ውጤቶች አሁን ባለው የትምህርት ስኬት እና የተግባር አፈጻጸም (Present Levels of Academic Achievement and Functional Performance) (PLAFP) ደረጃዎች፤ የ IEP ክፍል ውስጥ ተመዝግበው ይገኛሉ። ከሽግግር ምዘናዎች የተገኘው መረጃ የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግቦችን፣ የሽግግር ተግባራትን፣ አገልግሎቶችን፣ አመታዊ የ IEP ግቦችን እና የወኪል ድርጅቶች ግንኙነቶችን፤ እንዲሁም በሽግግር እቅድ ሂደት ውስጥ ቀጣይ እርምጃዎችን ጨምሮ ቀጣይነት ላለው የተማሪ የ IEP እድገት ሊያግዝ ይችላል። የግምገማ ውጤቶች ለተማሪ፣ ለቤተሰብ እና ለ IEP ቡድን መመሪያ እና አማራጮችን ይሰጣሉ።



## የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግቦች ፦

የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግቦች፤ ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ በድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ቅጥር፣ ትምህርት ወይም ስልጠና እና አስፈላጊ ከሆነ ራስን ችሎ በመኖር ዙሪያ ምን እንደሚያደርጉ፤ ራዕያቸውን ለይተው የሚያሳዩ መለካት የሚችሉ ግቦች ናቸው። የ IEP ቡድኖች የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግቦችን ከተማሪ እና ቤተሰብ ጋር ቢያንስ በየአመቱ በ IEP አመታዊ ስብሰባ ላይ ይወያያሉ። መለካት የሚችሉ የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ የስራ ቅጥር ግቦች በ IDEA ይጠየቃል።





## የጥናት ዘርፍ

የጥናት ዘርፍ ተማሪዎች የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግባቸውን ለማሳካት የሚያጠናቅቋቸውን ሁሉንም ክፍሎች እና የማህበረሰብ ተሞክሮዎችን ያካትታል። የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግቦች ተማሪዎች ከተመረቁ በኋላ መስራት፣ መማር እና መኖር የሚፈልጉበትን ቦታ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት። ከተማሪዎች ጋር የሚሰሩ ሁሉ፤ ከድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግቦቻቸው ጋር የሚጣጣም የጥናት ዘርፍ እንዲለዩ ማገዝ አስፈላጊ ነው። ቡድኑ በተማሪዎች ግቦች ላይ መሻሻልን በሚደግፉ ዘርፎች እና ተሞክሮዎች ላይ መሳተፍን ማረጋገጥ አለበት። በተማሪዎች የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግቦች እና በጥናት ዘርፉ መካከል ያለው ግንኙነት ግልጽ መሆን አለበት

የጥናት ዘርፍ፤ የተማሪዎችን የድህረ-ትምህርት ቤት ግቦች የሚደግፍ፤ የትምህርት እና የተግባር ውጤታቸውን ለማዳበር የተነደፈ፤ የተናጠል ኮርሶች፣ ተሞክሮዎች እና ስርአተ ትምህርት ስብስብ ነው።

## የሽግግር እንቅስቃሴዎች

የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር እንቅስቃሴዎች ተማሪዎች የድህረ-ትምህርት ግቦቻቸውን ለማሳካት እንዲረዳቸው የትምህርት እና የተግባር ክህሎቶቻቸውን ለማሻሻል የተነደፉ ናቸው። እነዚህ ተግባራት በልዩ ሁኔታ ለተማሪዎች የተነደፉት በጥንካሬዎቻቸው፣ በምርጫዎቻቸው፣ በፍላጎቶታቸው እና በሚያስፈልጓቸው ነገሮች ላይ በመመስረት ነው። እነሱም መመሪያን፣ ተዛማጅ አገልግሎቶችን፣ የማህበረሰብ ተሞክሮዎችን፣ የስራ ልማትን እና ራስን ችሎ የመኖር ክህሎት ማዳበርን ሊያካትቱ ይችላሉ። የሽግግር ተግባራትን በማስተዋል ማዘጋጀት እና መተግበር፤ ተማሪዎች ለግቦቻቸው ከመነሻ እስከ ስኬት ድረስ የሚወስዷቸውን እርምጃዎች ይፈጥራል።

**የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት (Career and Technical Education) (CTE)** ኮርሶች ሁሉንም ይጠቅማሉ፤ ነገር ግን CTE በተለይ የአካል ጉዳተኛ ተማሪን ይረዳል። መረጃው እንደሚያመለክተው በ CTE ክፍሎች የተመዘገቡ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች፤ ለመመረቅ እና የግዛት የብቃት ግቦችን የማሳካት እድላቸው ሰፊ ነው። በ CTE መርሃ-ግብሮች የተመዘገቡ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በ CTE መርሃ-ግብሮች ካልተመዘገቡ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የበለጠ የመመረቅ ቁጥር አላቸው።



## አመታዊ የ IEP ግቦች

አመታዊ የ IEP ግቦች ተዘጋጅተው የተጻፉት፤ተማሪዎች የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግባቸውን ለማሳካት የሚያስፈልጋቸውን እውቀት፣ ክህሎቶች እና/ወይም ባህሪያት እንዲገነቡ ለመርዳት ነው። አመታዊ የ IEP ግቦች እና የሽግግር ተግባራት፤ ትርጉም ወዳለው የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግቦች ስኬት የሚመራ ተማሪን ማዕከል ያደረገ IEP ለመፍጠር አብረው ይሰራሉ።

## የአዋቂ ዕድሜ

የአዋቂ ዕድሜ፤ አንድ ሰው ከሁሉም የአዋቂነት መብቶች እና ግዴታዎች ጋር እንደ አዋቂ ሰው የሚቆጠርበት ህጋዊ እድሜ ነው። በ Maryland ውስጥ የአዋቂ ዕድሜ 18 ዓመት ነው። ተማሪዎች 18 ዓመት ሳይሞላቸው ቢያንስ ከአንድ አመት፤ የ IEP ቡድን ስለ መብቶቻቸው ሽግግር እንዲያሳውቃቸው IDEA ያዛል። ተማሪዎች በ18 ዓመታቸው ሙሉ የውሳኔ ሰጪነት ኃላፊነትን ለመውሰድ ዝግጁ ካልሆኑ፤ ሌሎች አማራጮች አሉ፤ ለምሳሌ፤ ጥናት ሊደረግበት በሚችል ድጋፍ ውሳኔ መስጠት። በ Maryland ውስጥ፤ በውስን ሁኔታዎች ላይ ካልተመረኮዘ በስተቀር፤ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ውሳኔ ሰጪነት፤ በአዋቂ እድሜ ላይ ወዲያውኑ አይተላለፍም።

## ሞግዚትነት vs. በድጋፍ ውሳኔ መስጠት

ሞግዚትነት ፍርድ ቤት አንድን ሰው ወይም ወኪል ድርጅትን፤ ሌላ ሰውን ወክሎ ውሳኔ እንዲሰጥ የሚሾምበት ህጋዊ ሂደት ነው፤ እናም ለግለሰብ በጣም ገዳቢ የሆነ የህግ ጥበቃ አይነት ነው። በተለምዶ፤ በጣም ከባድ የሆነ የአእምሮ ጤና፣ የግንዛቤ ወይም የህክምና እክል ያለባቸው ግለሰቦች፤ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ በራሳቸው ማድረግ ካልቻሉ፤ የሞግዚትነት መስፈርቶችን ያሟላሉ። በ Maryland ውስጥ፤ አዲስ ህግ አሁን አዋቂዎች በድጋፍ ውሳኔ መስጠትን በመጠቀም፤ ለመረዳት፣ ግምት ውስጥ ለማስገባት እና ውሳኔዎችን ለራሳቸው እንዲወስኑ ይፈቅዳል። በድጋፍ ውሳኔ መስጠት፤ ግለሰቦች መብቶቻቸውን እንዲያስጠብቁ እና በህይወታቸው ላይ የበለጠ ቁጥጥር እና ምርጫ እንዲኖራቸው ይረዳል።





## ምርቃት

ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መመረቅ በእያንዳንዱ ተማሪ ህይወት ውስጥ ወሳኝ ምዕራፍ ነው። በ Maryland ውስጥ፤ ተማሪዎች የምዝገባ፣ የትምህርት ሰዓታትን እና የአገልግሎት መስፈርቶችን ካጠናቀቁ የ Maryland ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ማግኘት ይችላሉ። ለዲፕሎማ የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ማሟላት የማይችሉ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች፤ የ IEP ቡድኑ በ Maryland በተገለጸው የ Maryland ደንብ ውስጥ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎችን እንዳሟሉ ከወሰነ የ Marylandን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመርሃ-ግብር ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት ይቀበላሉ። ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የ Marylandን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመርሃ-ግብር ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት ለመስጠት፤ የተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መጨረሻ ድረስ ውሳኔ አይሰጥም።

## የ Maryland የአፈጻጸም ማጠቃለያ (Maryland Summary of Performance) (MSOP)

የ Maryland የአፈጻጸም ማጠቃለያ ስለ ተማሪዎች መረጃ የሚሰጥ ሪፖርት ነው፡-

- ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ስኬት፤
- ተግባራዊ አፈፃፀም፤
- ተስማሚ ነገሮች፤ እና
- በድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግቦች፣ አገልግሎቶች እና እንቅስቃሴዎች ላይ መሻሻል።




ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና የ IEP ቡድኖች መሻሻልን ለመገምገም እና በሽግግር እቅድ ሂደት ውስጥ ውሳኔዎችን ለመስጠት እና ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ወደ ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ እንቅስቃሴዎች ሲሸጋገሩ፤ በዚህ ሪፖርት ውስጥ ያለውን መረጃ መጠቀም ይችላሉ።
MSOP፤ አቅም ላላቸው ቀጣሪዎች፣ ለድህረ-ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ተቋማት እና ለአዋቂ አገልግሎት አቅራቢዎች፤ ስለ ወጣት አዋቂዎቹ ችሎታዎች፣ ጥንካሬዎች እና ስለሚያስፈልጓቸው ድጋፎች ትርጉም ያለው መረጃ ሊሰጥ ይችላል።

# የወኪል ድርጅት **ግንኙነት**

## መብት vs. ብቁነት-ልዩነቱ ምንድን ነው?

በ Maryland ውስጥ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት ብቁ የሆኑ ተማሪዎች፤ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ እስኪመረቁ ድረስ ወይም 21 ዓመት እስኪሞላቸው ያለው የትምህርት ዘመን ድረስ፤ የትምህርት አመቱ ከሃያ አንደኛው ዓመት ልደታቸው በፊት የሚጀምር ከሆነ፤ እነዚህን አገልግሎቶች የማግኘት መብት አላቸው። ግለሰቡ አሁን እነርሱን ለመቀበል ብቁ መሆናቸውን ለማየት ለአዋቂዎች አገልግሎት ማመልከት አለበት። ለአዋቂዎች አገልግሎት ብቁ መሆን መብት አይደለም እና አገልግሎቶችን የማግኘት ዋስትና አይሰጥም። ከአዋቂ አገልግሎት ወኪል ድርጅቶች አገልግሎቶችን እና ድጋፎችን ለመቀበል፤ የገንዘብ ድጋፍ መገኘት አለበት። ስለዚህ፤ የወኪል ድርጅቱን ብቁነት ለመወሰን የማመልከቻውን ሂደት ቀደም ብሎ መጀመር አስፈላጊ ነው።





## የ Maryland የአዋቂዎች አገልግሎት ወኪል ድርጅቶች

ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ በ Maryland ውስጥ ብቁ ለሆኑ ግለሰቦች አገልግሎቶችን ወይም ድጋፎችን ሊሰጡ የሚችሉ አራቱን የግዛት ወኪል ድርጅቶች ለይቶ ያሳያል። እያንዳንዱ ወኪል ድርጅት አገልግሎቶችን ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ልዩ የብቃት መስፈርቶች አሏቸው። እባክዎ አገልግሎቶችን ወይም የብቃት መመዘኛ ሂደታቸውን ስለሚመለከቱ ጥያቄዎች ተገቢውን ኤጀንሲ ያነጋግሩ።

### የመልሶ ማቋቋም አገልግሎቶች ክፍል (Division of Rehabilitation Services) (DORS)

የ Maryland መልሶ ማቋቋም አገልግሎት ክፍል (DORS) የአካል ጉዳተኞች ወደ ስራ እንዲሄዱ፣ በሥራ ላይ እንዲቆዩ ወይም ለስራው ዓለም እንዲዘጋጁ የሚያግዙ መርሃ-ግብሮችን ይሰጣል። DORS የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን፣ የኮሌጅ ተማሪዎችን እና በሌሎች የጸደቁ መርሃ-ግብሮች ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን፤ የሙያ ማማከር፣ አጋዥ ቴክኖሎጂ፣ የሙያ ስልጠና እና/ወይም የስራ ምደባ አገዛን ሊያካትቱ የሚችሉ አገልግሎቶችን በማቅረብ ወይም በማደራጀት ይረዳል።

ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ይጎብኙ፡- https://dors.maryland.gov/Pages/default.aspx

### የእድገት አካል ጉዳተኞች አስተዳደር (Developmental Disabilities Administration) (DDA)

የእድገት አካል ጉዳተኞች፤ የተቀናጀ ተወዳዳሪ የስራ ቅጥር ማግኘትን እና ማቆየትን ጨምሮ፤ በማህበረሰባቸው ውስጥ ሙሉ በሙሉ የመካተት ግብ ላይ ያተኮሩ ተገቢ አገልግሎቶች እንዲያገኙ፤ DDA የተቀናጀ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ያቀርባል። የ DDA የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት፤ የተለያዩ የቤት እና የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎቶችን እና ድጋፎችን በ በግዛት የ Medicaid እቅድ፣ Waiver program ወይም በ DDA የግዛት ገንዘብ ድጋፍ ጸልግሎቶች በኩል፤ ብቁ ለሆኑ ሰዎች የሚደረጉ ድጋፎችን ያካትታል።

ስለ DDA ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፡- https://dda.health.maryland.gov/Pages/dda.aspx

### የእድገት አካል ጉዳተኞች አስተዳደር (Developmental Disabilities Administration) (DDA)

BHA የአእምሮ ሕመም ያለባቸውን እና/ወይም የአልኮልና የመድኃኒት አጠቃቀም ችግር ያለባቸውን ሰዎች የሚያገለግል የ Maryland የጤና መምሪያ Maryland Department of Health (MDH) አካል ነው። በአካባቢያዊ የባህሪ አስተዳደሮች (Local Behavioral Administrations) (LBHA) ወይም ዋና ጸልግሎት ወኪል ድርጅቶች (Core Service Agencies) (CSA) በሚባሉት የአካባቢ ወኪል ድርጅቶች ኦማካኝነት፤ BHA ለመርሃ-ግብሮች የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል እናም ያስተዳድራል፤ በነዚህ ግን አይወሰንም፡- የአእምሮ ሕመምተኛ እንክብካቤ፣ የመኖሪያ ቤት ሕክምና፣ መደበኛ እና ከፍተኛ የተመላላሽ ሕክምና፣ የችግር ጊዜ አገልግሎቶች፣ የመልሶ ማቋቋም አገልግሎቶች፣ የቤተሰብ ድጋፍ፣ የአእምሮ ሕመም ላለባቸው ሰዎች የድጋፍ መኖሪያ ቤት እና የድጋፍ ቅጥር ስራ። በተለይ የሽግግር እድሜ ላላቸው ወጣቶች የተዘጋጁ መርሃ-ግብሮች በአንዳንድ አካባቢዎች ይገኛሉ።

ስለ BHA ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፡- https://bha.health.maryland.gov/pages/index.aspx

### የሰው ሀይል ልማት እና የአዋቂዎች ትምህርት ቢሮ፤ የ Maryland የስራ መምሪያ (የ Maryland ስራ)

የ Maryland የስራ መምሪያ፤ የሰው ሃይል ልማት ቢሮ፤ የወጣቶች አገልግሎት ክፍል፤ ወጣት አዋቂዎች የትምህርት እና የስራ ቅጥር ግቦቻቸው ላይ እንዲደርሱ ለመርዳት መርሃ-ግብሮችን እና አገልግሎቶችን ይሰጣል። በአካባቢ የ Maryland ስራ፤ የአሜሪካ የስራ ማእከላት እና የሰው ሃይል መዋዕለ ንዋይ ፍሰት ቦርዶች አማካኝነት፣ የ Maryland ስራ የሞያ ማማከር፣ ስልጠና፣ የኮምፒውተር ተደራሽነት እና ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶችን ይሰጣል። የ Maryland ስራ ከአሜሪካን የስራ ማእከላት ጋር በመጣመር የተለያዩ የቅጥር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤ እና ከስራ ሃይል ፈጠራ እና እድል ህግ (Workforce Innovation and Opportunity Act) (WIOA) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ደንበኞችን ከስራ ጋር የተዛመደ ስልጠና እና ከየትምህርት እድሎች ጋር ያገናኛል።

ስለ Maryland ሰራተኞች ለበለጠ መረጃ http://labor.maryland.gov

# **የሁለተኛ ድረጃ ሽግግር** የጊዜ ሰሌዳዎች

## 14 – 15 ዓመት እድሜ

ቤተሰቦች የሚከተሉትን ግንዛቤ ውስጥ በመክተት ተማሪያቸውን ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ ላለ ለህይወት ሊያዘጋጁ ይችላሉ።

- ከፍተኛ ግምቶችን ያዘጋጁ እና ይጠብቁ
- የሽግግር ምዘና ውጤቶችን ከተማሪዎ ጋር ይወያዩ
- የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግቦችን እና አማራጮችን ይወያዩ
- የተማሪዎን ጥንካሬያቸውን እና ግባቸውን ለማሳካት የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ያካፍሉ
- ስለ ቤተሰቡ የወደፊት ራዕይ አስተያየት ይስጡ
- የሙያ ፍላጎቶችን ለመመርመር እድሎችን ይስጡ
- ራስን መደገፍ፣ የጊዜ አስተዳደር እና የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታዎችን ለመለማመድ እድሎችን ይስጡ
- ከሽግግር ጋር የተያያዙ አውደ-ርዕዮች፣ የ IEP ስብሰባዎች እና ጉባኤዎች ላይ ይሳተፉ
- ተማሪዎን በ IEP ስብሰባዎቻቸው ላይ እንዲገኙ እና እንዲሳተፉ ያዘጋጁ
- ለስራ ቅጥር፣ ለትምህርት እና ለመዝናኛ ሁኔታዎች፤ የተግባቦት እና የማህበራዊ ክህሎቶችን ለማዳበር እና ለመለማመድ ያግዙ
- ከሽግግር ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን እና እንቅስቃሴዎችን መዝገብ ያስቀምጡ
- የተማሪዎን የአካል ጉዳት፣ መብቶች እና ኃላፊነቶች ይረዱ
- ተማሪዎን የአካል ጉድለታቸውን እና ጥንካሬዎቻቸውን እንዲረዱ ይምሩ
- በመምረጥ ውሳኔ የማድረግ እድሎችን ይስጡ
- የቅድመ-የስራ ቅጥር ሽግግር አገልግሎቶችን (Pre-Employment Transition Services) (PreETS) ከተማሪዎ እና ከ IEP ቡድን ጋር ይወያዩ
- ለአገልግሎቶች ብቁነትን ለመወሰን ለ DDA ያመልክቱ

## 16 – 17 ዓመት እድሜ

ለዚህ የዕድሜ ክልል ተጨማሪ ጉዳዮች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፦

- በትምህርት ቀን መገኘት፣ የክፍል ደረጃዎችን እና የማህበረሰብ አገልግሎት መስፈርቶችን ጨምሮ የምረቃ መስፈርቶችን እና መሻሻልን ይገምግሙ
- የትምህርት ተሞክሮዎችን፣ የስራ ቅጥር ዕድሎችን እና የማህበረሰብ ተሳትፎን ሊጨምሩ የሚችሉ አጋዥ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን መለየት
- የማህበረሰብ አገልግሎቶችን እና መርሃ-ግብሮችን መለየት
- በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ እና ከምርቃት በኋላ ስለ አገልግሎቶች ብቁነት ለማወቅ ከማህበረሰብ ወኪል ድርጅቶች ጋር ይገናኙ
- ስለ ድኅረ-ሁለተኛ ደረጃ መርሃ-ግብሮች እና የድጋፍ አገልግሎቶች መረጃ ይሰብስቡ
- አገልግሎቶችን ሊሰጡ ከሚችሉ ወኪል ድርጅቶች ጋር ለመገናኘት መፍቀዶን ለ IEP ቡድን ይፈርሙ
- ተማሪዎን የስራ እድሎችን በመመርመር እና በመሳተፍ ይደግፉ
- የአዋቂ እድሜን ከተማሪዎ ጋር ይወያዩ
- ሞግዚትነትን እና በድጋፍ ውሳኔ መስጠትን ይመርምሩ
- ከምርቃት በኋላ የመኳኋዣ አማራጮችን ይወያዩ
- እንደ ገንዘብ አስተዳደር፣ ጤናማ ኑሮ እና ራስን መንከባከብ ያሉ ራስን የመቻል ክህሎቶችን ያበረታቱ እና ይለማመዱ
- ከተመረቁ በኋላ መማር እንዴት እንደሚቀጥል ይወያዩ
- የ Marylandን የስራ አፈጻጸም ማጠቃለያ እና የተማሪዎ ወደ ግቦቹ ያለውን እድገት ይገምግሙ
- እንደአስፈላጊነቱ እና ብቁ ሲሆኑ ለ DORS፣ BHA እና MDL ያመልክቱ

## 17 – 18 ዓመት እድሜ

ለዚህ የዕድሜ ክልል ተጨማሪ ጉዳዮች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

- ስለ መመረቂያው ሂደት ተወያዩ
- ለመምረጥ መቼ መመዝገብ እንዳለባቸው ይወያዩ እና፤ ወንድ ከሆነ፤ ለተመረጠ አገልግሎት ይመዝገቡ
- የአዋቂ አገልግሎቶች ተደራሽነት መመሪያ እና ድጋፍ
- ተማሪዎ ውሳኔ እንዲያደርግ፣ ሀላፊነትን እንዲወስድ እና ከስህተቶች እንዲማር ይፍቀዱለት
- እንደ የስራ ልምምድ እና የሙያ እና የቴክኖሎጂ ትምህርት መርሃ-ግብሮች ባሉ በስራ ላይ የተመሰረተ የመማር እድሎች ላይ መሳተፍን ይወያዩ
- የወኪል ድርጅቶችን ወደ ሚመለከተው መምሪያ እና የአዋቂ አገልግሎቶች ማመልከቻዎችን ይከታተሉ
- እንደ ማህበራዊ ዋስትና እና ተጨማሪ የዋስትና ገቢ (Supplemental Security Income) (SSI) ያሉ፤ የከፍተኛ ትምህርት ወይም የቴክኒክ ትምህርት ቤት ድጋፍ አገልግሎቶችን እና የገንዘብ እርዳታ ድጋፎችን እና ጥቅማ ጥቅሞችን ለመወያየት የስብሰባ ቀጠሮ ያስይዙ
- ከምርቃት በኋላ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ወኪል ድርጅቶችን ወደ IEP ስብሰባ ለመጋበዝ ፈቃዶን ይፈርሙ
- ከተማሪዎ ጋር የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ይጎብኙ
- አስፈላጊ ከሆነ፤ በፌዴራል የተማሪ እርዳታ የነጻ ማመልከቻ (Free Application for Federal Student Aid) (FAFSA) ይሙሉ
- ስለ ድህረ-ትምህርት ቤት አገልግሎቶች ለመወያየት እና ለማቀድ ከ DORS አማካሪ ጋር ይገናኙ
- የተማሪዎን የ Maryland አፈጻጸም ማጠቃለያ ይገምግሙ እና የመጨረሻ ቅጂ ይውሰዱ
- የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ኮሌጆችን እና የስራ ቅጥር ማመልከቻዎችን እንዲያጠናቅቅ ተማሪዎን ይምሩ
- አስፈላጊ ከሆነ ተማሪዎ ለኮሌጅ እና ለትጥቅ አገልግሎት ፈተናዎች እንዲመዘገብ ያበረታቱ
- እንደአስፈላጊነቱ እና ብቁ ሲሆኑ ለ DORS፣ BHA እና MDL ያመልክቱ

## 18 – 21 ዓመት እድሜ

ለዚህ የዕድሜ ክልል ተጨማሪ ጉዳዮች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

- እንደ የኮሌጅ ግቢ ያሉ፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሽግግር መርሃ-ግብሮች ላይ፤ ለእድሜ ተገቢ በሆነ መልኩ ለመወያየት ከ IEP ቡድን ጋር ይገናኙ
- የድህረ-ትምህርት ቤት ግቦችን ስኬት የሚደግፉ ክፍሎች ውስጥ መመዝገብን እና አካታች ተሳትፎን ያበረታቱ
- በማህበረሰብ ስራ እና በመማር ተሞክሮዎች ውስጥ ተሳትፎን ይደግፉ
- የመጓጓዣ አማራጮችን ለመማር እና ለመለማመድ እድሎች ይስጡ
- ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ የሚያስፈልጉትን ድጋፎች ይለዩ
- ለአዋቂ አገልግሎቶች ብቁነትን ያረጋግጡ
- ወደ አዋቂ አገልግሎቶች የሚደረገውን ሽግግር ለማገዝ ከ DDA የማህበረሰብ አገልግሎቶች ማስተባበሪያ ጋር ይገናኙ
- ተማሪዎን ለ SSI፣ ለሕክምና እዛ እና ለአካል ጉዳተኞች የጋራ መጓጓዣ አገልግሎቶች እንዲያመለክቱ ይደግፉ
- አስፈላጊ ከሆነ፤ በ2024 የትምህርት ዘመን የሚጀመረውን የ Maryland የመርሃ-ግብር ማጠናቀቂያ የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ድጋፎችን ከ IEP ቡድን ጋር ይወያዩ
- እንደአስፈላጊነቱ እና ብቁ ሲሆኑ ለ DORS፣ BHA እና MDL ያመልክቱ



# ተቀዳሚ 10 ነገሮች

## ወላጆች **ልጃቸውን ለሁለተኛ ደረጃ ሽግግር** እንዲዘጋጁ ማገዝ ይችላሉ

1 የወጣትዎን የአካል ጉዳት ይረዱ። ወጣትዎን ሊያውቁ ይችላሉ፤ ነገር ግን የወጣትዎ አካል ጉዳት በመማር፣ በተግባቦት ወይም በእንቅስቃሴ ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያደርስበት ወይም እንደሚያደርስባት ያውቃሉ? በሽግግር እቅድ ወቅት፤ የወጣትዎን የአካል ጉዳት እና የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ክትትልን፣ የስራ ቅጥርን ወይም እራስን ችሎ ለመኖር እንዴት ተጽእኖ እንደሚያደርስ በተሻለ ለመረዳት ይሞክሩ።

2 ወጣትነትዎ ስለ ራእሱ ወይም ራሷ የወደፊት ራዕይ እንዲፈጥሩ ያበረታቱ። ያንን ራዕይ እንዲገነዘቡ እና የእሱን ወይም የእሷን የልምድ መሰረት ለማስፋት ወጣትዎን አማራጮችዎን እንዲመረምሩ እርዷቸው። ይህ አስፈላጊ ከሆነ፤ ዘርፍን የመቀየር ነፃነትን በመገንባት ወጣቶችዎ የሽግግር እቅድ ሂደቱን በባለቤትነት እንዲይዙ ያስችላቸዋል።

3 ወጣቶችዎ ራዕያቸው እውን ሊሆን እንደሚችል እንዲገነዘቡ ይርዷቸው።  ወጣቶች ከራሳቸው ምን እንደሚጠብቁ ከወላጆች ፍንጭ ያገኛሉ።  የ IEP የሽግግር እቅድ ራዕያቸውን ለማሳካት እና ግባቸው ላይ ለመድረስ መንገድ እንደሆነ በወጣትዎ ውስጥ ያሳድሩ።

4 ለወጣትዎ የከፍተኛ ተስፋ እምነትን ይገንቡ። ወጣትዎ ከፍተኛውን ችሎታውን ወይም ችሎታዋን ሊያሳኩ እንደሚችሉ ከፍተኛ ተስፋ ሊኖርዎት ይችላል። እነዚያን ተስፋዎች ለ IEP እና ለሽግግር እቅድ በማንፀባረቅ መሟገት ያስፈልጎታል። ለወጣትዎ ያሎት የወደፊት ተስፋ ዝቅተኛ ከሆነ፤ ሌሎችም እንዲሁ ሊያደርጉ ይችላሉ።

5 በ IEP ስብሰባዎች ወቅት ጥንካሬዎችን፣ ፍላጎቶችን እና የሚያስፈልጉ ነገሮችን በመናገር ስለወጣትዎ የሚያውቁትን ያጋሩ። መምህራን እንደዚህ አይነት የወላጆችን መረጃ ከፍ አድርገው ይመለከቱታል ምክንያቱም ግምገማዎች እና የትምህርት ቤት ምልከታዎች ማሳየት የማይችሉትን ዝርዝሮች ለማቅረብ ይረዳል። ይህ መረጃ የ IEP ቡድንን የተማሪን ፍላጎት ወይም የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን የማይመለከቱ የትምህርት እና የአገልግሎት ውሳኔዎችን እንዲያስቀር ሊረዳው ይችላል።



6 የወጣትዎን አስፈላጊ የትምህርት መዝገቦችን በሙሉ ያስቀምጡ። ወላጆች እንደ የሪፖርት ካርዶች፣ ወቅታዊ እና ያለፉ የ IEP ሰነዶች እና የግምገማ ማጠቃለያ ሪፖርቶች የመሳሰሉ የልዩ ፍላጎት ትምህርትን ለማቀድ የሚጠቅሙ አስፈላጊ የሆኑ መዝገቦችን በተደራጀ መንገድ ማስቀመጥ አለባቸው።

7 የ IEP ሂደትን በመጠቀም የወጣትዎን በራስ መተማመን እና የራስን ዕድል በራስ መወሰንን ይገንቡ። ሃሳባቸውን የሚገልጹበት ውጤታማ መንገድ እንዲያገኙ ይርዷቸው። በ IEP ስብሰባ ላይ ስለራሳቸው ሊናገሩ ወይም ፓወርፖይንት ወይም ቪዲዮ ሊያዘጋጁ ይችላሉ።

8 ወጣቶችዎ በመማር፣ ጥናት በማድረግ እና በአኗኗር ችሎታዎች ላይ ራሳቸውን መቻል እንዲያዳብሩ ይርዷቸው። እንደ አዳዲስ ነገሮችን ለመማር መጓጓት፣ ጊዜን በብቃት መምራት እና መልካም ስራ ለመስራት ሀላፊነትን መውሰድ የመሳሰሉ አዎንታዊ ባህሪያት፤ ወጣቶችን በስራ ቅጥር፣ በድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና በማህበረሰብ ተሳትፎ ረገድ በጥሩ ሁኔታ ይጠቅማሉ።

9 "ለስላሳ ክህሎቶች" በስራ ቅጥር እና በትምህርት ስኬት ላይ ያላቸውን ተጽእኖ ይረዱ፤ እናም እነዚህን ክህሎቶች ለመገንባት በቤት ውስጥ እንቅስቃሴዎችን ይጠቀሙ። ለስላሳ ክህሎቶች፣ ግላዊ ተግባቦት እና ኃላፊነት፤ ሁሉም ሰው ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልገው መሳሪያዎች ናቸው። ወጣትዎቹን ከሌሎች ጋር እንዴት በትክክል መግባባት እንደሚችሉ፤ የግል ገጽታን እንዲጠብቁ፤ የስራ አቅጣጫ እንዲይዙ እና ግጭቶችን መፍታት ያስተምሯቸው።

10 ለወጣቶችዎ ሊሆኑ የሚችሉ የማህበረሰብ ድጋፎችን እና የስራ እድሎችን በመለየት ያግዙ። ይህ ከመልሶ ማቋቋሚያ አገልግሎቸች ክፍል የቅጥር እርዳታን፤ በኮሌጅ የተማሪዎች የአካል ጉዳተኝነት አገልግሎቶች ጽህፈት ቤት አማካኝነት የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ድጋፎችን፤ ወይም በማህበረሰብ አቀፍ ድርጅት የሚሰጡ ገለልተኛ የኑሮ ክህሎቶች ትምህርትን ሊያካትት ይችላል። ወላጆች ያሉትን አማራጮች በደንብ ማወቅ እና የእነዚህ አገልግሎቶች ተወካዮች በ IEP ስብሰባ ላይ እንዲገኙ፤ ወይም ለቡድኑ መረጃ እንዲሰጡ መጠየቅ አለባቸው።

*ከ PACER የተወሰደ" የአካል ጉዳተኛ ልጅዎን ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ ላለው ህይወት የሚያዘጋጅ መመሪያ።"

# ግብዓቶች

**Got Transition**
www.gottransition.org/

Got Transition በፌዴራል የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት፤ ከህጻናት ህክምና እስከ የአዋቂዎች የጤና እንክብካቤ የሚደረገውን ሽግግር ለማሻሻል ዓላማ ያለው፤ የብሔራዊ የጤና አጠባበቅ ሽግግር የመርጃ ማዕከል ነው። ወጣት አዋቂዎችን፣ ቤተሰቦችን እና ተንከባካቢዎችን፤ ለተሳካ የአዋቂዎች የጤና እንክብካቤ ሽግግር ለማዘጋጀት፤ መሳሪያዎች፣ ግብዓቶች፣ እና መረጃዎች ተካትተዋል።

**የ Maryland የእድገት አካል ጉዳተኞች ምክር ቤት፦ በድጋፍ ውሳኔ መስጠት**
www.md-council.org/did-you-know-a-new-supported-decision-making-bill-just-passed-in-maryland/

ይህ ጽሑፍ፤ የአዋቂዎችን ድጋፍን በማግኘት አዋቂዎች በድጋፍ ውሳኔ እንዲወስኑ እና የራሳቸውን ውሳኔ እንዲሰጡ፤ በ Maryland የሚደገፍ ውሳኔ አሰጣጥ ህግን ለማብራራት ግልጽ ቋንቋ ይጠቀማል።

**Maryland MTA Disability Reduced Fare Program**
www.mta.maryland.gov/disability-reduced-fare-program

የ Maryland የመጓጓዣ አስተዳደር (Maryland Transit Administration) (MTA)፤ የአካል ጉዳተኞች ቅናሽ ዋጋ መርሃ-ግብር ብቁነት ተብራርቷል። የበይነ መረብ ማመልከቻ በቅጾች ገጽ ላይ፤ በቅናሽ ዋጋዎች ስር ይገኛል።

**Maryland MTA MobilityLink**
www.mta.maryland.gov/mobility

MTA MobilityLink፤ የ MTAን ቋሚ መስመር ስርዓትን መጠቀም ለማይችሉ የአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች፤ የ paratransit program ነው። ማመልከቻውን ለመሙላት ማስፈንጠሪያ እና የአካል ጉዳተኞች የጋራ መጓጓዣ አገልግሎቶች መመሪያ ተካትቷል።

**የ Maryland ግዛት የትምህርት መምሪያ፤ የአካል ጉዳተኞች የሁለተኛ ደረጃ የሽግግር እቅድ መመሪያ**
elevates.marylandpublicschools.org/secondary-transition-planning-guide/

ይህ መመሪያ ስለ ሁለተኛ ደረጃ ሽግግር ሂደት ለተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ አስተማሪዎች እና የማህበረሰብ ወኪል ድርጅቶች መረጃ ይሰጣል። ከሁለተኛ ደረጃ የሽግግር እቅድ አካላት ጋር የተያያዙ የህግ መስፈርቶች፣ ስልቶች እና ግብዓቶች ተካትተዋል። መመሪያውን በ20 ተጨማሪ ቋንቋዎች ለማግኘት ማስፈንጠሪያ ተካቷል።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና የሽግግር ብሔራዊ ማዕከል**
www.ncset.org/

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና የሽግግር ብሔራዊ ማዕከል (National Center on Secondary Education and Transition) (NCSET) የተቋቋመው የአካል ጉዳተኛ ወጣቶች የተሳካ የአዋቂ ውጤት እንዲያገኙ ዕድሎችን ለመፍጠር ነው። ድህረ ገጹ በሁለተኛ ደረጃ ሽግግር ዙሪያ አስተማሪዎችን፣ ቤተሰቦችን እና ተማሪዎችን ለመደገፍ ግብዓቶችን ያቀርባል።



**ብሔራዊ የሰው ኃይል እና የአካል ጉዳተኝነት ትብብር**

youth.gov/federal-links/national-collaborative-workforce-and-disability

ይህ ድህረ ገጽ፤ ተማሪዎች ወደ አዋቂ ህይወት በሚያደርጉት ሽግግር እና ቤተሰቦች እና ወጣት አዋቂዎች ብዙ ጊዜ ከሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች ጋር በተያያዙ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የመረጃ ምንጭ ነው። ተማሪዎችን እና የሽግግር ዕድሜ ወጣቶች ያሏቸውን ቤተሰቦች ለመደገፍ፤ ለአካል ጉዳተኛ ወጣቶች የሚሆኑ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ማስፈንጠሪያዎች ተካትተዋል።

**ብሔራዊ የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር የቴክኒክ ድጋፍ ማዕከል**

www.nsttac.org

ድህረ ገጹ ሁሉንም የሁለተኛ ደረጃ የሽግግር ጉዳዮችን የሚዳስሱ መሳሪያዎችን እና ግብዓቶችን፤ ለአስተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ለተማሪዎች ያቀርባል። የሽግግር እቅድን ለመደገፍ የበይነ-ግንኙነት ማስፈንጠሪያዎች ተካተዋል።

**የ PACER ማእከል ብሔራዊ የሽግግር እና የስራ ቅጥር የወላጆች ማእከል**

www.pacer.org/tatra

የ PACER ማእከል፤ ከ14 እስከ 21 ዓመት እድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ የአካል ጉዳተኛ ወጣት አዋቂ ወላጆች፤ ከሽግግር ጋር በተያያዙ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መረጃን፣ ግብዓቶችን እና የቴክኒክ እርዳታ ይሰጣል። ይህ ለአጠቃቀም ቀላል የሆነ ድህረ ገጽ ከወላጅ እይታ የሚነሱ ጥያቄዎችን እና ስጋቶችን ለመፍታት፤ በወላጆች የተዘጋጁ ግብዓቶችን እና ምክሮችን ይሰጣል።

**Think College**

www.thinkcollege.net

Think College የአእምሮ ውስንነት ላለባቸው ተማሪዎች ሁሉን አቀፍ የከፍተኛ ትምህርት አማራጮችን ለማዳበር፣ ለማስፋት እና ለማሻሻል የሚሰራ ብሔራዊ ድርጅት ነው። ድህረ ገጹ ለተማሪዎች እና ቤተሰቦች የኮሌጅ አማራጮችን፣ ለኮሌጅ እንዴት እንደሚዘጋጁ እና የመግቢያ ሂደቱን በተመለከተ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ መረጃን ይሰጣል።

# የሁለተኛ ደረጃ የቃላት መፍቻ
# **የሽግግር ውሎች**

**ተስማሚ ነገሮች**
በመስፈርቱ ወይም በሚጠበቀው ተግባር ላይ መሰረታዊ ለውጥ ሳያስፈልግ፤ ሙሉ ተደራሽነት እና የእውቀት ትክክለኛ ማሳያ የሚፈቅድ፤ ከተማሪው የአካል ጉዳት ጋር የተያያዘ አገልግሎት ወይም ድጋፍ።

**የአቃቂ አገልግሎቶች**
ሰዎች ለአካለ መጠን ሲደርሱ የሚያስፈልጉ አገልግሎቶች፤ ስራ ለማግኘት የሚደረግ እገዛ፣ በቤት ውስጥ የሚደረግ እርዳታ፣ ከስራ ቅጥር ጋር የተያያዙ እንደ መኖሪያ ቤት እና መጓጓዣ እና የተለያዩ ሕክምናዎችን ወይም መድኃኒቶችን የማድረስ እገዛ፤ ብዙ ጊዜ እነዚህን ቢያጠቃልሉም፤ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይወሰኑም።

**ለእድሜ ተገቢ የሽግግር ግምገማ**
የተማሪዎችን የሚያስፈልጉ ነገሮች፣ ምርጫዎች እና ፍላጎቶች ከወቅታዊ እና የወደፊት ስራ፣ ትምህርት፣ ኑሮ እና የግል እና ማህበራዊ አከባቢ ጋር በሚገናኝ መልኩ ቀጣይነት ያለው መረጃዎችን የመሰብሰብ ሂደት።

**የአዋቂ ዕድሜ**
አንድ ሰው ከሁሉም የአዋቂነት መብቶች እና ግዴታዎች ጋር እንደ አዋቂ ሰው የሚቆጠርበት በህጋዊ መንገድ የተገለጸ እድሜ ነው። ይህ Maryland ውስጥ 18 ዓመት ነው።

**የአካል ጉዳተኛ የአሜሪካዊያን ህግ (Americans with Disabilities Act ) (ADA)**
የአካል ጉዳተኞችን መሰረታዊ የሲቪል መብቶች የሚያረጋግጥ የፌዴራል የአካል ጉዳተኞች ፀረ-መድልዎ ህግ። ይህ በዘር፣ በጾታ፣ በብሔር ማንነት እና በሃይማኖት ለግለሰቦች ከሚቀርበው ጋር ተመሳሳይ ነው። በስራ፣ በትራንስፖርት፣ በመንግሥት አገልግሎቶች ወ.ዘ.ተ ለአካል ጉዳተኞች የእኩል እድል ዋስትና ይሰጣል።

**የ Maryland የስራ ልምምድ**
የ Maryland የስራ ልምምድ፤ እድሜያቸው 16 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ተማሪዎች የወጣቶች የስራ ልምምድ መርሃ-ግብር ነው። በምርት እና በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በምህንድስና እና በሂሳብ (Science, Technology, Engineering, and Mathematics) (STEM) ሙያዎች ወይም በ CTE የሞያ ክላስተር ውስጥ ያሉ ሌሎች ሙያዎች ላይ መሰረት በማድረግ ወደ ዘላቂ የስራ ቅጥር እና ተጨማሪ ትምህርት እንዲመራ የተነደፈ ነው።

**ረዳት የቴክኖሎጂ (Assistive Technology) (AT) መሳሪያ**
የአካል ጉዳተኞችን የተግባር አቅም የሚጨምር፣ የሚጠብቅ ወይም የሚያሻሽል፤ ለንግድ አገልግሎት የተዘጋጀ፣ የተሻሻለ ወይም የተበጀ ማንኛውም እቃ፣ የመሳሪያ ቁራጭ፣ ወይም የምርት ስርዓት።

**የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት (Career and Technical Education) (CTE)**
ለወደፊት በሙያ ስኬታማ እንዲሆኑ እና በተዛማጅ የቴክኒክ እውቀት እና ክህሎቶች ብቁ እንዲሆኑ፤ ለተማሪዎች የአካዳሚክ እና የቴክኒክ ክህሎቶች፤ እውቀት እና ስልጠና የሚሰጡ ተከታታይ ኮርሶች።

**የሙያ አሰሳ**
የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሙያ አማራጮችን የሚፈትሹበት እና ተማሪዎች ልዩ ፍላጎቶቻቸውን፣ ችሎታዎቻቸውን እና ተሰጥኦዎቻቸውን እንዲለዩ በሚያግዙ በተለያዩ ግምገማዎች እና እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚሳተፉበት ሂደት።

**በማህበረሰብ ላይ የተመሰረተ መመሪያ**
እንደ የትምህርት ስርአተ-ትምህርታቸው እና የትምህርት አሰጣጣቸው አካል ተማሪዎችን ወደ ማህበረሰባቸው መቀላቀል።

**በማህበረሰብ ላይ የተመሰረቱ አገልግሎቶች**

በማህበረሰብ ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶች፤ በተለይም በግለሰቡ የመኖሪያ ማህበረሰብ ውስጥ።

**ተወዳዳሪ የሥራ ስምሪት**

ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከወጡ በኋላ በሙሉ ወይም በትርፍ ጊዜ ስራ ቢያንስ በዝቅተኛ የጉልበት ዋጋ ወይም ተመጣጣኝ በሆነ ክፍያ መስራት፡- (ሀ) የተቀናጀ ተወዳዳሪ የቅጥር ሁኔታ (ለ) ወታደራዊ (ሐ) በማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍ የቅጥር ሁኔታ (መ) የቤተሰብ ንግድ (ለምሳሌ፤ እርሻ) (ሠ) የራስ ስራ

**የትምህርት ዘርፍ**

የተማሪውን ለድህረ-ትምህርት ቤት የታለሙ ግቦችን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ የባለብዙ-ዓመት የኮርስ ስራ መግለጫ።

**የዕለት ተዕለት ኑሮ ችሎታዎች**

ለዕለታዊ ተግባራት የሚያስፈልጉ ክህሎቶች፤ ማለትም መብላት፣ መልበስ፣ ማጠብ፣ ንጽህናን መጠበቅ፣ መጸዳጃ ቤት መጠቀም።

**ተግባራዊ የህይወት ክህሎቶች**

በተቻለ መጠን ራስን ችሎ ለመኖር የሚያስፈልጉ ክህሎቶች። ምሳሌዎች ማህበራዊ ክህሎቶችን፣ ተግባቦትን፣ ባህሪን እና የደህንነት ክህሎቶችን ያካትታሉ።

**ተግባራዊ የሙያ ግምገማ**

በተጨባጭ ወይም በተመሰለ የስራ ሁኔታ ውስጥ ወይም በተጨባጭ የስራ ናሙና ተሞክሮዎች ውስጥ፤ የተማሪን ጥንካሬዎች፣ ችሎታዎች እና አስፈላጊ ነገሮች ለመወሰን የሚደረግ ግምገማ።

**ራስን ችሎ የመኖር ክህሎቶች**

አዋቂ ሰው በተሳካ ሁኔታ ራስን በመቻል ተግባራትን እንዲፈጽም አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ችሎታዎች ወይም ተግባራት። የትርፍ ጊዜን፣ የቤት ጥገና እና የግል እንክብካቤን እና የማህበረሰብ ተሳትፎን ሊዳስሱ ይችላሉ።

**የግለሰብ የስራ ቅጥር እቅድ (Individualized Plan for Employment) (IPE)**

የአካል ጉዳተኛን ሰው ወደ ተወዳዳሪ የስራ ተቀጣሪነት የሚመራውን እቅድ የሚገልጽ ሕጋዊ ሰነድ። በመልሶ ማቋቋም አገልግሎቶች ክፍል ጥቅም ላይ ይውላል።

**የተቀናጀ ወይም የሚደገፍ ስራ ቅጥር**

የአካል ጉዳተኛ ግለሰብ ስራውን ለመማር እና ለማስጠበቅ፤ አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያገኝበት የስራ ሁኔታ።

**የፍላጎት ቆጠራ**

የአንድን ሰው ፍላጎቶች፣ መውደዶች እና አለመውደዶች ከእንቅስቃሴዎች እና ሊሆኑ ከሚችሉ የሙያ አማራጮች ጋር የሚያዛምድ፤ በሙያ እቅድ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ራስን የመገምገሚያ መሳሪያ።

**የስራ ትንተና**

አንድን የተወሰነ ስራ በማጠናቀቅ ውስጥ የተካተቱትን የተወሰኑ ተግባራትን እና ንዑስ ተግባራትን መለየት።

**የስራ አሰልጣኝ**

አንድ ግለሰብ ስራ እንዲማር ወይም እንዲቀጥል እገዛ የሚያደርግ ሰው፤ የስራ ቦታ ስልጠና እና ድጋፍን ሊያካትት ይችላል።

**የስራ ናሙና**

ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚ ሊሆኑ የሚችሉትን ስራዎች ለመወሰን፤ የግለሰቡን ችሎታ እና ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት፤ በተለያዩ ስራዎች ላይ "እጃቸውን እንዲፈትሹ" እድል መስጠት።

**የስራ ክትትል**

የተለያዩ ስራዎችን እና የስራ አካባቢ አይነቶችን በመከታተል እና ስራዎችን የሚሰሩ ሰዎችን በመመልከት መመርመር።

**የህይወት ክህሎቶች**

ቤትን ለማስተዳደር፣ ለማብሰል፣ ለመገበያየት፣ ፋይናንስ ለማስተዳደር እና የግል የመኖሪያ አካባቢዎችን ለማደራጀት የሚያገለግሉ ማናቸውም ችሎታዎች።

**መካሪ**

በወጣቶች ወይም በወጣት አዋቂዎች እና፤ ድጋፍ፣ መመሪያ እና እርዳታ በሚሰጥ በእድሜ እና በተሞክሮ በሚበልጥ ሰው መካከል ያለ ደጋፊ ግንኙነት።

**የመንቀሳቀስ ችሎታዎች**

ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሰላም የመጓዝ ችሎታ።

**የስራ ላይ - ስልጠና**

አንድ ሰው በስራ ቦታ ላይ እያለ፤ ከነባሩ የስራ ድርሻ ጋር በተያያዘ በሚያደርጋቸው አንዳንድ ተግባራት፤ የሚያገኘው እውቀትና ክህሎቶች ናቸው።

**የሚከፈልበት ስራ**

ለሌላ ሰው ወይም ለንግድ ስራ የሚሰራ ሰው ክፍያ።

**ሰውን ማዕከል ያደረገ እቅድ ማውጣት**

አካል ጉዳተኞች ህይወታቸውን እንዲያቅዱ፣ ድምፃቸውን እንዲያገኙ እና ግባቸው ላይ ለመድረስ እንዲሰሩ የሚያስችል ሂደት። በጥንካሬያቸው እና በምርጫዎቻቸው ላይ ያተኩራል.

**ራስን መደገፍ**

የሰዎችን የአካል ጉዳት መረዳት፣ ከአካል ጉዳታቸው የሚመጡትን ጥንካሬዎች እና ድክመቶች ማወቅ እና የሚያስፈልጓቸውን የተወሰኑ ተስማሚ ነገሮች ማስረዳት መቻል። ተሟጋችነት ሰዎች፤ ስለሚያስፈልጓችው ነገሮች እና ምርጫዎች የመናገር ችሎታ ነው።

# ጥያቄዎች ካሉኝ ወይም እርዳታ ቢያስፈልገኝስ?
# **እርዳታ ያስፈልጎታል?**

## የአካባቢ የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች አስተባባሪዎች

| የአካባቢ ትምህርት ቤት ስርዓት | ከ ልደት እስከ 5 ዓመት | ከ 5 እስከ 21 ዓመት |
|---|---|---|
| Allegany | 240-920-6829 | 240-920-6829 |
| Anne Arundel | 410-424-3270 | 410-424-3258 |
| Baltimore City | 410-396-1666 | 443-642-3848 |
| Baltimore County | 443-809-9696 | 443-809-5443 |
| Calvert | 443-550-8406 | 443-550-8375 |
| Caroline | 410-479-3609 | 410-479-3609 |
| Carroll | 410-751-3955 | 410-751-3955 |
| Cecil | 410-996-6230 | 410-996-6230 |
| Charles | 301-934-7456 | 301-934-7456 |
| Dorchester | 410-901-6915 | 410-901-6915 |
| Frederick | 240-578-1244 | 240-236-8744 |
| Garrett | 301-914-1351 | 301-914-1351 |
| Harford | 410-273-5579 | 410-273-5579 |
| Howard | 410-313-7161 | 410-313-7161 |
| Kent | 410-778-5708 | 410-778-5708 |
| Montgomery | 240-777-4809 | 240-753-9487 |
| Prince George's | 240-521-5054 | 301-431-5675 |
| Queen Anne's | 410-758-2403, x135 | 410-758-2403, x135 |
| Somerset | 410-651-1616, x11385 | 410-651-1616, x11385 |
| St. Mary's | 301-475-5511, x32218 | 240-309-4113 |
| Talbot | 410-822-0330 | 410-822-0330 |
| Washington | 301-766-8221 | 301-766-8221 |
| Wicomico | 410-677-5250 | 410-677-5250 |
| Worcester | 410-632-5234 | 410-632-5234 |
| የ Maryland የአይነ ስውራን ትምህርት ቤት | 410-444-5000, x1489 | |
| የ Maryland መስማት የተሳናቸው ትምህርት ቤት | 443-277-8899 | |
| የ Maryland ግዛት የትምህርት መምሪያ | 410-767-0255 | |

**የ MARYLAND ግዛት የትምህርት መምሪያ**

**Mohammed Choudhury**
የግዛት ትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ

**Dr. Deann Collins**
የማስተማር እና መማር ቢሮ ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ

**Clarence C. Crawford**
ፕሬዝዳንት፤ የ Maryland ግዛት የትምህርት ቦርድ

**Wes Moore**
አስተዳዳሪ

© 2023 Maryland State Department of Education
ይህ ህትመት የተዘጋጀው በ Maryland ግዛት የትምህርት መምሪያ፤ የቅድመ ጣልቃ ገብነት ክፍል እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ከ U.S. በተገኘ ገንዘብ ድጋፍ ነው። የትምህርት ክፍል፤ የገንዘብ ድጋፍ #H393A090124A፤ የልዩ ፍላጎት ትምህርት የገንዘብ ድጋፍ ለህፃናት እና ቤተሰቦች "የማገገሚያ የገንዘብ ድጋፎች" በ PL 105-17/111-5 መሰረት የአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች የትምህርት ህግ/የአሜሪካ ማገገሚያ እና መልሶ ማልማት ህግ። የ Maryland ግዛት የትምህርት መምሪያ፤ የቅድሚያ ጣልቃገብነት ክፍል እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች፤ ለ Maryland ሕፃናት እና ታዳጊዎች መርሃ-ግብር መሪ ወኪል ድርጅት ነው፤ በግዛት እና በአካባቢ ወኪል ድርጅቶች እና በድርጅቶች የተቀናጁ የግዛት አቀፍ የአገልግሎት መርሃ-ግብሮች እና ድጋፎች። በዚህ ህትመት ውስጥ ያለውን መረጃ የሚያባዙ ወይም የሚያጋሩ ተጠቃሚዎች ለ Maryland ግዛት የትምህርት መምሪያ፣ የቅድመ ጣልቃ ገብነት እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ክፍል እውቅና መስጠት አለባቸው፤ Dr. Deann Collins፤ የማስተማር እና መማር ቢሮ ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ



MARYLAND STATE DEPARTMENT OF
EDUCATION
EQUITY AND EXCELLENCE

410-767-0100

www.marylandpublicschools.org

200 West Baltimore Street
Baltimore, MD 21201-2595